# እንኳን ለአንድ መቶ ሀያ አንደኛው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዐል አደረሰን።

*　*　*　*

## የታደሉት

የወረራው ግዙፍነት
የዘመቻው ትልቅነት
የትግሉ መራራነት
የድሉ ጣፋጭነት . . .
እየገረመኝ
እያስደነቀኝ
ለማወቅ ስሻ ምስጢሩን
ወርቅ-ለበስ ትርጉሙን
ሆኖ አገኘሁት የጠለቀ
ከጀግንነት የረቀቀ።
ከሰማዕትነቱ፣ ከመሥዋዕትነቱ ጀርባ
ከጦር ሜዳው ባሻገር ከትንቅንቁ አምባ
ቃልኪዳን ይዘው ነው የዘመቱ
እምነታቸውን አንግበው የጽናት ነጋሪት እየመቱ።
ጉልበታቸውን ያገዘፈው
ወኔያቸውን ያጋለው
ጦራቸውን ያሾለው
ጐራዴያቸውን የሳለው
ጋሻቸውን ያጠጠረው
ጉዟቸውን ያከበረው . . .
እምነታቸው ነው ጽናታቸው
የትውልድ ቃል ኪዳናቸው።
የነፃነት ውርስ ለማቆየት
ባለራዕይ ትውልድ ለማየት
ፈልገው ነው የሞቱላት
የቆሰሉ የደሙላት . . .
ለኢትዮጵያ
የተሠዉ ለክብሯ . . .
በአድዋ።

___________________

ቴዎድሮስ አበበ
Washington, DC